# የአስተማሪ አድናቆት መግለጫ /ቪዲዮ/ ሜይ 9

የአስተማሪ የምስጋና ሳምንትን ስናከብር፣ አስተማሪዎች ለተማሪዎቻችን እና ለት/ቤቶቻችን ማህበረሰቦች የሚያበረክቱትን አስደናቂ እሴት ለመግለጽ ትንሽ ጊዜ መውሰድ እፈልጋለሁ። መምህራን የትምህርት ስርዓታችን የልብ ትርታ በመሆናቸው፣በሚያደርጉት ትጋት እና በጥረታቸው በተማሪዎቻችን ህይወት ላይ እውነተኛ ለውጥ ያመጣሉ። ይህን የሚያደርጉት ከሁሉም የት/ቤቶቻችን መሪዎች እና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች ጋር ነው።

ተማሪዎቻችን በአካዴሚያዊ፣ በማህበራዊ እና በስሜታዊ እሴቶች በልጽገው እንዲያድጉ ለመርዳት መምህራን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይሰራሉ። ከእናንተ አንዷ ስለነበርኩ ይህን አውቃለሁ።

አስተማሪዎች የማወቅ ጉጉትን ያነሳሱ፣ የመማር ፍቅርን ያቀጣጥላሉ፣ እና ተማሪዎች የሚበለጽጉበት ምቹ አካባቢን ይፈጥራሉ። የእነሱ አዎንታዊ ተፅእኖ ከክፍል ውስጥ ያለፈ በጣም ሩቅ ነው፥ የወደፊት የሕብረተሰብ መሪዎችን ይቀርፃሉ።

እኔና የእኔ ቡድን በምንታገልለት የስራ ማስኬጃ በጀት ውስጥ፣ ለመምህራን የሚገባቸውን ክብር ለመስጠት ረጅም ርቀት የሚሄድ  የደመወዝ ንድፈሀሳብ አቅርበናል።

ለዚህ ነው ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያቀረበውን ሙሉ ባጀት/ገንዘብ እንዲመድቡ እና ለመምህራኖቻችን እውነተኛ አድናቆት እንዲያሳዩ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስልን የማሳስበው። በመምህራኖቻችን ላይ ኢንቨስት ማድረግ በተማሪዎቻችን እና በማህበረሰባችን የወደፊት ሁኔታ ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ነው።

አስደናቂ መምህራኖቻችን በሙሉ ለተማሪዎቻችን ስላሳያችሁት የማያወላውል ቁርጠኝነት እናመሰግናለን። የእናንተ ትጋት እና ጥረታችሁ ሳይስተዋል አይታለፍም።

መልካም የመምህራን አድናቆት ሳምንት!